የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
Ginbot 7: Movement for Justice Freedom and Democracy
Tel +44 208 1335670 pr@ginbot7.org

---

**<u>የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከሴምቴምበር 17- 18, 2010 ያካሄደውን 2ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ መጠናቀቅን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ።</u>**

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ከተለያዩ ክፍለ አለማት በተወከሉ የግንቦት 7 አባላት አማካኝነት ጠቅላላ ጉባኤውን በተሳካ መልኩ አካሂዶል። በዚህ የ2 ቀን ውሎ ጉባኤ የድርጅቱን የ 2 አመት የስራ ክንዋኔ ገምግሟል፡፡ የንቅናቄውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመመልከት ጥንካሬውን የበለጠ ለማጥበቅ ድክመቶችን ለማረም እና ለማስወገድ አስተላልፎአል። ሆኖም ግን ይህ የሁለት ቀን ጉባኤ ከማናቸውም ጉዳይ በላይ ትኩረት የሰጠው ነጥብ እየገዘፈ የሄደውን የወያኔን ፀረ- ኢትዮጵያ ፣ ዘረኛና አምባገነናዊ አመለካከቱና ድርጊቱ ላይ ነው።

ጉባኤው፡ ዛሬ በሀገራችን የነገሰው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ረጅም ታሪክ ውስጥ በአምባገነንነቱ፤ በዘራፊነቱ ፤በዘረኝነቱና በፀረ-ኢትዮጵያዊነቱ ተወዳዳሪ የሌለው አገዛዝ ነው በማለት ፈርጆታል።

ይህ አገዛዝ እየዋለና እያደረ ዘረኝነቱን ወርቅ በሚለው ህዝብ አሻግሮ፣ ወርቅ በሚለው ጎጥ ላይ አራምዶ፣ወርቅ ወደሚለው ዘረኛ ቤተሰብ አውርዶታል። አምባገነንነቱንም ሳያቋርጥ በወሰዳቸው የግዲያና የእመቃ እርምጃዎች፤ እንዲሁም በአወጣቸው ፍጹም አፋኝ ህጎች አማካኝነት ባገኘው 99.6፥ የፓርላማ መቀመጫ ባለቤትነት አስረግጦታል።
ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ ድርጊቱ፤ ቀደምት ኢትዮጵያውያን አጥንታቸውን ከስክሰው፣ ደማቸውን አፍሰው ያስከበሩትን እና ያነበሩትን ለም መሬት ለባእድ መንግስታት ከመስጠት አልፎ፣ የተቀረውን የሀገሪቱን መሬት ለባእዳን በመሸጥ የሀገሩን ዜጋ በገዛ ሀገሩ የባእዳን ባሪያ እስከ መሆን አድርሶታል።
የንቅናቄው ጉባኤ ይህ በወያኔ የተፈጠረ እጅግ አሳሳቢ የሆነ ከዜጎች መብትና ጥቅም መገፈፍ ፣እንዲሁም ከሀገር ህልውና ጋር የተሳሰረ አደጋ እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱ አሳሳቢ ሆኖ አግኝቶታል። ከዚህም በመነሳት፡-

1. ጠቅላላ ጉባኤው የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራር፡ ይህንን ዘረኛና ፀረ-ሀገር የሆነውን የወያኔ ቡድን ለማንበርከክ፣ ሀገርንና ህዝብን ነፃ ለማውጣት ማንኛውንም አይነት ስልት፣ ዘዴና እርምጃ መውሰድ እንዲችል ሙሉ ውክልና ሰጥቶታል
2. ይህን ሁሉንም የሀገሪቱን ዜጎች ክብር የገፈፈና ያዋረደ ዘረኛ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ምድር ለመጥረግ በዲሞክራሲ ከሚያምኑ እና በወያኔ ዘረኝነት ከተንገፈገፉ ሀይሎች ጋር በመተባበር በጋራ እንዲሰራ ሙሉ ውክልና ሰጥቶታል፡;

ጉባኤው በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የሚገኘው፣ ነፃነቱን፤ ሀገሩንና ክብሩን የሚወድ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከግንቦት 7 ንቅናቄ እና ከንቅናቄው ጋር በፀረ ወያኔነት ትግል ከተሰለፉ ሀይሎች ጎን በመቆም ማንኛውንም አይነት ተሳትፎ እና ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪውን በማቅረብ ስብሰባውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቋል።

“ውድመት ለዘራፊ ዘረኞች
ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!
ሴምቴምበር 19, 2010